# ሕያው እምነት፡ ናዛሪኖች ምን ያምናሉ

በዘመናችን ያለ ማንኛውም ድርጅት ጽኑ የሆነ የጋራ ዓላማ፣ እምነት እና እሴቶች ልኖሩት ያስፈልጋል። የናዛሪን ቤተ ክርስቲያንም እነዚህ ነገሮች አሏት። ቤተ ክርስቲያኒቷ የተመሠረተችው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅድስና በማስፋፋት ዓለምን ለመለወጥ ነው። ይህች ቤተ ክርስቲያን በአንድ ጊዜ የታላቁን ተልዕኮ ለመፈጸም የተዘጋጀች እንዲሁም የቅድስና ቤተ ክርስቲያን ናት። ተልዕኮአችንም በዓለም ሁሉ ውስጥ ክርስቶስን የሚመስሉ ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ነው።

የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን የአሁንም ሆነ የወደፊት ሁኔታ የሚወሰነው የእግዚአብሔርን ተልዕኮ ለመፈጸም በሚታደርገው ተሳትፎ ነው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያንቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን መገለጫ ናት እንዲሁም ልዩ የሚያደርጋት እምነቷ ብቻ ሳይሆን ለእግዚብሔር መንግስት የሚታበረክተው የተለየ መሆኑ ጭምር ነው።

እንደ ናዛሪን ቤተ ክርስቲያንነታችን ወደ አዲስ ምዕተ አመት ስንሰጋገር የእኛነታችን መለያ የሆኑትን ነገሮችን ለይተ ማወቅና ማክበር ይጠበቅብናል። ዋናው ሀብታችን- ተልዕኮአችን፣ ጥሪያችን፣ እምነቶቻችን እና ዕሴቶቻችን ናቸው- ለሚቀጥለውም ትውልድ እነዚህን ነገሮች ስናስረክብ በደስታ ነው።

ማዕከላዊ ዕሴቶቻን ለወደፊት የሚመጡት አመታት ምሪት የሚሰጡ ብርሃኖች ሆነው ማገልገላቸውን ይቀጥሉ ዘንድ ጸሎታችን ነው።

### ማዕከላዊ ዕሴቶቻችን

### 1. እኛ ክርስቲያኖች ነን

እንደ ዓለም አቀፋ ቤተ ክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት የሚያውጁና በክርስትና እምነት መገለጫ የተጻፈውን በአሃዱ ሥሉስ የሚቀበሉ እውነተኛ አማኞች ጋር እንስማማለን። የእኛ የሆነው የዌዝልያዊያ- ቅድስናዊ ትውፊ ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን እንዲሁም እውነተኛ እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ምክንያት፣ ትውፊት እና ልምምድ የሚገኝ መሆንን እንገነዘባለን።

### 2. እኛ የቅድስና ሕዝቦች ነን

ቅዱስ የሆነው እግዘኢብሔር ቅዱስ የሆነ ሕይወት እንድኖር ጠርቶናል። መንፈስ ቅዱስ በሁለተኛ የጸጋ ሥራ አማካኝነት በእኛ ውስጥ ለመሥራት እንደጠራን እናምናን። ይህም ሥራ በተለያዩ ስሞች ይጠራል፤ ሁለተናዊ መቀደስ እና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ሲሆን በዚህም ከኃጢአት ሁሉ ነጽተን፣ የእግዚአብሔር መልክ ታድሶ፣ እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን፣ ነፍሳችን፣ አእምሮዋችን እና ኃይላችን እንዲሁም ባልንጀራችንን እንደራሳችን መውደድ ያስችለናል፤ ከዚህ በተጨማር በእኛ ውስጥ የክርስቶስን ባሕርይ ይፈጥራል። በአማኞች ውስጥ ያለው ቅድስና በትክክለኛ መንገድ ስንረዳተው ክርስቶስን መምሰል ነው።

### 3. እኛ የተልዕኮ ሰዎች ነን

እኛ የተላክን ሰዎች ነን፣ ለክርስቶስ ጥሪ ምላሽ የሰጠን እና ወደ ዓለም ሁሉ ለመሄድ የ፣ምፈስ ቅዱስ ኃይልን የተቀበልን፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ጌትነት ለማወጅ እና ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት እና መንግስቱን ለማስፋት ከእግዚብሔር ጋር የምንተባበር ሕዘቦች ነን (2 ቆሮ

6፡1)። ተልዕኮአችን (ሀ) በአምልኮ ይጀምራል፣ (ለ) በወንጌል ስርጭትና በርኅራኄ ዓለምን እናገለግላለን፣ (ሐ) ክርስቲያኖችን በደቀ መዝሙርነት ወደ ክርስቲያናዊ ብስለት እንዲደርሱ እናበረታታለን እናም (መ) በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትምህርት ክርስቲያን ወንዶችና ሴቶችን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ብቁ እንዲሆኑ እናደርጋለን።

*ማብራሪያ*

## 1. እኛ ክርስቲያኖች ነን

የኢየሱን ክርስቶስን ጌትነና ከሚያውጁ አማኞች ጋር አንድነት አለን፡፤ በመለኮታዊ ፍቅር አማካኝነቱ እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ የኃጢአት ይቅርታ መስጠቱንና ከእርሱ ጋር ግንኙነት ማደስ እንደሚችሉ እናምናለን። ከእግዚብሔር ጋር ከታረቅን እርስ በእርሳችንም ሰላም እንደሚነረን እናምናለን፣ በእግዚአብሔር እንደ ተወደድን እርስ በእርሳችን መዋደድ እንዳለብን፣ እግዚአብሔር ይቅር እንዳለን እርስ በእርሳችን ይቅር ልንባበል እንደሚገባ እናምናለን። እኛ በአንድነት የሚኖረን ሕይወት የክርስቶስ ባሕርይ ምሳሌ እንደሆነ እናምናለን። በክርስትና እምነት መግለጫ የተጻፈውን በአሃዱ ሥሉስ የሚቀበሉ እውነተኛ አማኞች ጋር እንስማማለን። የእኛ የሆነው የዌዝልያዊያ- ቅድስናዊ ትውፊ ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን እንዲሁም እውነተኛ እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ምክንያት፣ ትውፊት እና ልምምድ የሚገኝ መሆንን እንገነዘባለን።

ከሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በመሆን ኢየሱስ ጌታ መሆኑን እናውጃለን።

ኢየሱ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ጌታ ነው፣ የሐዋርያት የእመነት መግለጫ እንዳስቀመጠው ቤተ ክርስቲያን አንድ፣ ቅዱስ፣ ዓለም አቀፋዊ እና ሐዋርያዊት ናት። በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እግዚአብሔር የኃጢአት ይቅርታን አዘጋጅቶልናል እንዲሁም ከዓለም ጋር መታረቂያ መንገድን አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ስጦታ በእምነት የተቀበለ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይሆናል። በክርስቶስ ይቅር ከተባልንና ከታረቅን በኋላ እርስ በእረሳችን ይቅር እንባባላለን እንዲሁም እርቅም በመካከላችን ይወርዳል። በዚህ መንገድ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እና አካል እንሆናለን እንዲሁም የአካሉን አንድነት እንገልጻለን። እንደ ክርስቶስ አንድ አካልነታችን እኛ ‹‹አንድ ጌታ፥ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ።›› (ኤፌ 4፡5፣3) የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አንድነት እንቀበላለን እንዲሁም ይህንን አንድነት ለመጠበቅ የበኩላችን ጥረት እናደርጋለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጌታ ነው። ስለዚህም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንድ ብቻ ሳትሆን ቅዱስም ናት። በሁለተናዋ ቅዱስ መሆን ይጠበቅባታል፣ ራሱ ቅዱስ ስለሆነ አካሏም ቅዱስ መሆን አለበት። ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ናት እንዲሁም ቅዱስ ለመሆን ተጠርታለች፡፤ ቅዱስ የሆነቸው ለእኛ ጸድቅና ቅድስና የሆነ የክርስቶስ አካል በመሆኗ ምክንያት ነው፡፤ ቅዱስ ለመሆን የተጠራቸው በእግዚብሔር ሲሆን፣ እግዚብሔርም ዓለም ሳይፈጠር በፊት ቅዱስና ያለነቀፋ ትሆን ዘንድ መርጧታል፡፤ እንደ ክርስቶስ አንድ አካልነታችን እንደ ቤተ ክርስቲያን የሚኖር አንድነት የክርስቶስን ሙሉ ባሕርይ የሚያሳይ ለሆን ይገባዋል፤ ክርስቶስ ራሱን ባዱ በማድር የባሪያን መልክ ይዞ ነበር። የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ቅድስና እንደ ስጦታ እና ጥር አድርገን እንቀበላለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ጌታ ነው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን አንድ እና ቅዱስ ብቻ ሳትሆን ዓለም አቀፋዊም ናት። ማለትም በውስጧ የክርስትና መሠረታዊ እምነቶችን የሚቀበሉትን ሁሉ ታቅፋለች። በሁሉም ክርስቲያኖች፣ በየትም ቦታ እና በዬትኛውም ዘመን ያሉ እና የነበሩ ተቀባይነት ያለውን የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ እምነትን እንቀበላለን። የዌዚልን ዓለማቀፋዊ መንፈስ እንቀበላለን፤ በዚህም የመጸሐፍ ቅዱስን ማዕከላዊነት የሚቀበሉትን ጋር እንስማማለን እንዲሁም ከደንነት ጋር ተዛማጅነት ባሌላሸው ጉዳዮች ከእኛ ጋር ከማይስማሙት ጋር ተቻችለን እንኖራለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጽሐፍ ቅዱሱ ጌታ ነው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲን አንድ፣ ቅዱስ እና ዓለም አቀፋዊ ብቻ ሳትሆን ሐዋርያዊት ናት። ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት እና በነብያት መሠረት ላይ የተመሠረተች ናት እንዲሁም በቀጣይነት ለሐዋርያት ትምህርትን የምታስተምር ናት። ቤተ ክርስቲያናችን የቤተ ክርስቲያን የእምነት እና የአኗኗር መመሪያ ምንጭ የሆነውን መጸሐፍ ቅዱስን ብቻ እንደሆነ ታምናለች። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጌታ በመሆኑ መትኸፍ ቅዱሽን መረዳት ያለብን መንፈስ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ በሚመሰክረው መሠረት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረዳታችንን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ እና ለማስተካከል ወደ ጥንነታዊ የእምነት መግለጫዎች እና ሌሎች መጽሐፍ ቅዱስን በታማኝነት ወደሚያብራሩ ክርስናዊ ትውፊቶች እንመለከታለን። ከዚህ በተጨማሪ የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ ምሪትን እንከተላለን። በመጨረሻም የመጸሐፍ ቅዱስ መረዳታችንን ትክክለኝነት በአምክኖአዊነቱ እና ከሌሎች ስለ ኢየሱስ ከምመሰክሩ ነገሮች ጋር አብሮ መሄዱን እንፈትናለን።

የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ቅድስና በዌዚልያን ቅድስና ትውፊት አማካኝነት ለማወጀት ልዩ በሆነ መንገድ ተጠርተናል። ደንነት በጸጋ አማካኝነት በኢየሱ ክርስቶስነ በማመን ብቻ እንደሚገኝ እናምናለን። ይህንምም በማድረግ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አንድ፣ ዓለማቀፋዊ እና ሐዋርያዊት እንደሆነች እንቀበላለን። ነገር ግን የእኛ ልዩ ጥሪ በዓለም እና በቤተ ክርስቲያን ሁሉ ፊት የቅድስናን ማዕከላዊነት እንዲሁም የእግዚብሔር ሕዝብ በአባቱ የቅድስና ፍቅር ሙላት መኖርን እንድናሳይ ነው። በዚህም ምክንያት የዌዚልያን-ቅድስና የክርስቲያናዊ መረዳተን እንቀበላለን እንዲሁም ለመሠረታዊ አስምህሮዎቹም ታማኞች ነን፤ እርሱም፤- የእግዚብሔር የቅድመ ደንነት ጸጋ፣ የአዲስ ውልደት፣ መጽደቅ፣ ማረጋገጫ፣ የክርስቲያናዊ ማህበረሰብ እና ደቀመዛሙርቱ እንዲሁም ፍጹም ፍቅር ናቸው።

## 2. የቅድስና ሕዝቦች ነን

በእግዚአብሔርን ለማምለክ እና በሙሉ ልባችን፣ ነፍሳችን፣ አእምሮዋችን እና ኃይላችን እግዘአብሔርን ለመውደድ እንዲሁም ባለንጀራችንን እንደ ራሳችን ለመውደድ መጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት የተጠራን እና በጸጋው ወደ እርሱ የተጠጋን ሰዎች ነን። በሁለተኛ የጸጋ ሥራ አማካኝነት ‹‹ሙሉ ለሙሉ እንቀደሳለን›› ብለን በማመን ለዚህም ግብ ራሳችንን ሙሉ ለሙሉ እና ፈጽመን ለእግዚአብሔር የሰጠን ነው። መንፈስ ቅዱስ እንደሚወቅስ፣ እንደሚያነጻ፣ እንደሚሞላና በኃይል እንደሚያስታጥቅ እናምናለን። ይህም የእግዚብሔር ጸጋ ከቀን ወደ ቀን ሰዎች እንድንወድ እና የደቀመዝሙርነት ሕይወታችን፣ ስነ ምግባራዊ እና ግብረገባዊ ንጽሕናችንን እና ለሰዎች ያለንን ርኅራሄ እና ለፍትሕ ያለንን ለውጥ እየለወጠን ይመጣል። የእግዚአብሔር መልክ በእኛ ውስጥ የማደስ ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው

እንዲሁም ይህ መንፈስ የክርስቶስን ባሕርይ በእኛ ውስጥ ይፈጥራል። በአማኞች ውስጥ የሚታየው ቅድስና ክርስቶስን የሚመስል ነው።

ፈጣሪ በሆነው፣ ያሌለውን ነገር እንድኖር አድርጎ በፈጠረው በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። እኛ በአንድ ወቅት አልነበርንም ነገርግን እግዚአብሔር ወደ ሕያውነት ጥርቶናል፣ ለራሱ ዓላማ ሠርቶናል እንዲሁም በራሱ መልክ አበጅቶናል። የእግዚአብሔር መልክ እንሸከም ዘንድ ተልዕኮ ተሰጥቶናል፡ ‹‹[44]እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ፤ እኔ ቅዱስ ስለ ሆንኩ እናንተም ራሳችሁን የተቀደሰ አድርጉ፤ በደረታቸው እየተሳቡ የሚንቀሳቀሱትን ነፍሳት በመብላት ራሳችሁን አታርክሱ።›› (ዘሌ 11፡44)

ሪሃባችን እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ ቅዱስ ሕዝቦች መሆን ነው። የእግዚአብሔር ቅድስና የእርሱን መለኮታዊነት፣ የእርሱን አንድነት ያመለክታል። በክብርና በግርማ እርሱን የሚመስለው የለም። እንዲህ ባለው የክብር ግረማ ሞገስ በተጎናጸፈው አምላክ ፍት የሰው ልጅ ምለሽ  እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ ማምለክ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቅድስና የተገለጠው በትልቅ ሰዎች ማዳን በምችል ጸጋ ነው። እግዚአብሔር ራሱን የገለጠውና እንዲያመልኩት የፈቀደው ለዚህ ነው። ያመልኩት ዘንድ። ቅዱስ፣ አዳኝ ጌታን የሚወደውን እየወደድን እናመልከዋለን።

ታላቁና በጸጋ የተሞላውን እግዚአብሔርን የምናመልክበት መንገድ የተለያየ ነው። ብዙ ጊዜ ከእምነት ማህበረሰቡ ጋር በመሆን በአንድት እንዘምራለን እንዲሁም እንጸልያል። ከዚህ በተጨማር በገል የጥሞና ጊዜ በምናቀርበው የምስጋና እና እርሱን መታዘዝ ይገለጣል። ለሰዎችን ወንጌልን መመስከር፣ ለተቸገሩት የርኅራሄ አገልግሎት መስጠት፣ ለፍትሕ መስፈን መስራት እና ግብረገባዊ ሆኖ መኖር የአምልኮ ናቸው። ከዚህ በተጨማር በየዕለቱ የሚናደርጋቸው ነገሮች እንኳ አምልኮ ልሆኑ ይችላሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ቅዱስ አምላክን ገልጾልናል። እንዲሁም እንዴት እርሱን ማምለክ እንደምቻል በምሳሌነት አሳይቶናል። ኢየሱስ የቅድስናን ምንነት በሕይወቱ ኖሮ፣ መስዋዕት ሆኖ አሳይቶና፤ ይህም በወንጌላት መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል። እንደ ቅድስና ሕዝቦች በእያንዳንዱ አመለካከታችንና ተግባራችን ኢየሱስን መምሰል እንፈልጋለን። በጸጋው አማካኝት እርሱን በሙሉ ልባቸው የሚያመልኩ አማኞች ክርስቶስን የሚመስል ሕይወትን ይኖራሉ። የቅድስና መሠረታዊ ሀሳብ ይህ እንደሆነ እንገነዘባለን።

እግዚአብሔር ስጦታንና የመመርጥ ኃላፊነትንም ሰጥቶናል። ምክንያቱም የምንወለደው ኃጢአት መሥራት ዝንባሌ ኖሮን ነው፤ ከእግዚብሔር መንገድ ይልቅ የራሳችንን መንገድ ለመምረጥ እናዘነብላለን (ኢሳ 53፡6)። በኃጢአታችን የእግዚብሔርን ፍጥረታት ከአበላሸን በኋላ ፣ በኃጢአታችን እና በበደላችን ምክንያት ሙታኖች ነበርን (ኤፌ 2፡1)። ያሌለውን ነገር ወደ መኖር ባመጣው እግዚአብሔር አማካኝነት ወደ መንፈሳዊ ሕያውነት ተጠራን፣ በልጁ የመዋጀት ሥራ በጸጋው እኛን አድስ አድርጎ ፈጠረን።

እግዚአብሔር ልዩ በሆነ መንገድ በቅዱስ ልጁ አማካኝነት ትስበእት ሆነ ወደ ምድራችን መጣ። የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ ታሪካዊው አምላክ-ሰው ሆነ። ኢየሱስ በእኛ ውስጥ የእግዚአብሔርን ለማደስ፣ ቅዱስ የእርሱ ሕዝቦች መሆን እንችል ዘንድ መጥቷል። በአማኞች ዘንድ ልኖር የሚገባው ቅድስና ቅጽበታዊ እና ሂደታዊ ቅድስና እንደሆነ

እናምናለን፡፡ ከዳግም ውልደትን ተከትሎ የጌታ መንፈስ ለእርሱ ሕይወታችን አሳልፈን መስጠት እንድንችል ይመራናል፡፡ ከዚያም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተብሎ በምጠራው የመለኮታዊ ተግባር ሁለተናዊ ቅድስናን እንደምንለማመድ እናምናለን፡፡ በዚህም ከውርስ ኃጢአት እርሱ ያነጻናል እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በውስጣችን ያድራል፡፡ በፍቅር ፍጹማን ያድረገናል፣ ግብረገባዊ ሆነን እንድንኖር ያድረገናል እና ለአገልግሎት ያስታጥቀናል፡፡

የኢየሱስ መንፈስ በውስጣችን በመሥራት ቅዱስ ፍቅር የሆነው የእርሱ ባሕርይ በእኛ ውስጥ ይፈጥራል፡፡ "[24]በእውነተኛ ጽድቅና ቅድስና በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰውነት ልበሱ።" እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ኢየሱሰን መምሰል ማለት ነው፡፡ በእግዚብሔር የሁለትናን የሚቀድስ ተግባር የእግዚብሔር መልክ በውስጣችን ከታደሰ በኋላ መንፈሳዊነት ላይ ገና አለመድረሳችን እንገነዘባለን፣ የሕይወታችን ግብ የሚሆነው በእያንዳንዱ ቃል፣ ሀሳብ እና ተግባር ክርስቶስን መምሰል ይሆናል፡፡ በአንድ ማህበረ ምእመን ውስጥ እንዳለ ሰው ክርስቶስን የምመሰል ማህበረሰብ ለመፍጠር እንጥራለን፣ በሙሉ ልባችን እግዚብሔርን ለማምለክ እና የፍቅር፣ የንጽሕና፣ ያኃይል እና የርኅራሄ ስጦታውን ለመቀበል እንጥራለን፡፡

እንደ ቅድስና ሕዝቦች በታሪካዊ እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ አንኖርም፡፡ ራሳችንን ከአዲስ ኪዳንና ከቀደምት ቤተ ክርስቲያናት ጋር እናመሳስላለን፡፡ የእምነተ መግለጫችንም ከጥንታዊያን ክርስቲያኖች በጋር ያስቀምጠናል፡፡ ከአርሜናዊያን ነጻ ጸጋ ትውፊት ጋር ያመሳስለናል (ኢየሱስ የሞተው ለሁም ነው) እንዲሁም የሰው ልጆች ነጻ ፈቃድ እንዳላቸው እናምናለን፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ የመምረጥ ነጻነት እንዳላቸው እና መዳን እንደምችሉ እናምናለን፡፡ ከዚህ በተጨማር የቤተ ክርስቲያናችን እምነተን በ18ኛው ክፍለ ዘመን እና በ19ኛው እና በ20ኛ ው ክፍለ ዘመን ከተነሳው የቅድስና ከዌዚልያን መቃቃት የተያያዘ ነው፡፡

በዘመናት ውስጥ የቅድስና ሕዝቦች ከኢየሱስ ጋር ትልቅ ፍቅር ይዞዋቸዋል፡፡ ኢየሱስን እናመልካለን! ኢየሱስን እንወደዋለን! ስለ ኢየሱስ ሁል ጊዜ እናስባለን! ስለ ኢየሱስ እናወራለን! ኢየሱስን እንኖረዋለን! ለእኛ የቅድስና ይዘት እና ከዚያ የሚፈሰው ነገር ይህ ነው፡፡ የቅድስና ሕዝቦች መለያ ባሕርይ ይህ ነው፡፡

## 3. የተልዕኮ ሕዝቦች ነን

### 3ሀ. የመምለክ ተልዕኮአችን

ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያላት ተልዕኮ የጀመረው በአምልኮ ነው፡፡ የእግዚብሔር ሕዝቦች መሆናችንን በግልጽ የሚታወቀው አንድ ላይ ተሰባስበን እግዚአብሔር- በመዝሙር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስነበብ ስንሰማ፣ አስራታችንን እና መባችንን ስንሰጥ፣ ስንጸልይ፣ ስብከት ስንሰማ፣ ስናጠምቅ እና የጌታ እራትን አብረን ስንቀበል ነው፡፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያለው ሥራ የሚፈጸመው እኛ በአንድነት ተሰባስበን በማምለክ እና አዳዲስ ሰዎችን ወደ ህብረታችን በማስገባትና አዳዲስ የአምልኮ ስፍራዎችን በማዘጋጀት እንደሆነ እናምናለን፡፧

አምልኮ እግዚአብሔርን መውደዳችን መግለጫ ትልቁ መንገድ ነው፡፡ በጸጋው እና በምህረቱ የዋጀንን አምላክ እናመልካለን እንዲሁም እናደንቃለን፡፡ አምልኮ ልደረግበት የሚገባው ዋነኛው ሥፍራ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ራሳቸውን ከፍ ከፍ ለማድረግ ሳይሆን የእግዚብሔር ሕዝቦች ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት የሚጥሉበት እና ራሳቸውን መስዋእት ለማድረግ የሚሰባሰቡበት ስፍራ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያነው ውስጥ እግዚብሔርን ማመልክ ለእግዚብሔር ያለንን ፍቅር እና እርሱን ለማገልገል ያለንን መታዘዝ ያሳያል፡፡

አምልኮ የእግዚአብሔር ሕዝብ ዋነኛ ዕድል እና ኃላፊነት ነው፡፡ አምልኮ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ የእርሱን ማንነት፣ ምን እንዳደረጋ እና የተስፋ ቃሉ ምን እንደሆነ ለማወጅ የምሰባሰቡበት ነው፡፡

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚደረግ አምልኮ ማዕከላዊ የማንነታችን መገለጫ ነው፡፡ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምልኮ የሚያድረጉ ሰዎች ስብስብ ነው፡፡ በአጥቢያ ቤተ ክርስያን ውስጥ እና በኩል ነው ተልዕኮአችንን የምንፈጽመው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በመስበክ፣ የቤተ ክርስቲያን ስረዓቶችን በመፈጸም፣ መጸሐፍ ቅዱስን በጋር በማንበብ፣ አብሮ በመዘመር፣ በጋራ በመጸለይ እና አስራታችንን እና መባችንን በመስጠት የእግዚአብሐየር ሕዝቦች እንደሆንን እንገነዘባለን፡፡ በዚህ መንገድ ስናመለክ በእግዚብሔር የደንነት ሥራ ውስጥ ተሳትፎ እያድረግ እንደሆነ እናውቃለን፡፧

የአምልኮ ተልዕኮአችን ለቤተ ክርስቲያናችን መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ እንደ ናዛሪን ቤተ ክርስያን እኛ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እናመልካን፣ የአምልኮ ተልዕኮአችንም አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናትን መጀመርንም ያካትታል፡፡

**3ለ. የርኅራኄ እና የወንጌል ስርጭት ተልዕኮአችን**

እንደ እግዚብሔር ሕዝብ እኛ ለእግዚብሔር የተሰጠን ነን፣ የእርሱ ፍቅር ለጠፉት፣ ለተቸገሩ እና ለተሰበሩት እናሳያለን፡፡ ታላቁ ተልዕኮ እና ታላቁ ትዕዛዝ በወንጌል ስርጭት፣ ርኅራኄ እና ፍትሕ ላይ ተሳትፎ እንድናደረግ ይገፋፋናል፡፡ እስከ አሁን ድረስ ሰዎችን እንዲያምኑ እንጠይቃለን፣ የተቸገሩትን እንረዳለን፣ ፍትሕን እንድሠፍን እንሰራለን እንዲሁም የእግዚአብሔር ፍጥረት ለመንከባከብ እንሠራለን እንዲሁም የእግዚአብሔርን ስም የሚጠሩ ሰዎችን ሁሉ በሕብረታችን ውስጥ እናቅፋለን፡፡

በዚህ ተልዕኮአችን ቤተ ክርስቲያናችን ለእግዚአብሔር ያላትን ፍቅር ታሳያለች፡፡ የመጸሐፍ ቅዱስ ታሪክ እግዚአብሔር ዓለም ሁሉ ከራሱ ጋር ለማሳታረቅ ያደረገው ነገር ታሪክ ነው፣ በመጨረሻም በኢየሱስ ክርስቶስ (2 ቆሮ 5፡16-21) ይህንን ፈጽሞታል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም በዚህ የፍቅር እና የእርቅ አገልግሎት በወንጌል ስርጭት፣ በርኅራኄ እና በፍትሕን በማስፈን ትሳተፍ ዘንድ ተጠርታለች፡፡

ታላቁ ተልዕኮ እና ታላቁ ትዕዛዝ ሁለቱም የቤተ ክርስቲያናችን ተልዕኮ ለመረዳት አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ሁለቱም የአንድ ተልዕኮ መገለጫዎች ናቸው፣ የአንድ ወንጌል ሁለት አንጻር ናቸው፡፡ በማቴ 22፡37፣ 39 ላይ እግዘኢብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ ሀሳብ እና አእምሮህ ውደድ እንዲሁም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ብሎ ያዘዘው ኢየሱስ ወደ

ዓለም ሁሉ ሂዱና በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ እያጠመቃቸሁ ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቻ በማለት አዟል። (ማቴ 28፡19-20)

በዓለም ውስጥ ወደ አሉት በእግዚአብሐየር አምሳል የተፈጠሩት ሰዎች የመድረስ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጣ ተልዕኮ ትልቅ ዋጋ አለው። እግዚአብሔር እንደወደዳቸው እና ዋጋ እንደሰጣቸው ሰዎችን መውደድ እና ለእነርሱ ዋጋ መስጠት ተልዕኮአችን ነው። እግዚብሔር ሰለምን፣ ፍትሕን እና ድንነትን በክርስቶስ አማካኝነት ሰጥቷል። የተቸገሩትን መርዳትና ርኅራሄ ማሳየት የእኛ ተልዕኮ ነው። የሰዎችን ማንነት የሚያዋርዱ ማህበረሰቫዊ እስቶችን መቃወም ተልዕኮአችን ነው።

የቤተ ክርስቲያናችን ተልዕኮ የሰውን ሁለተና ያካትታል። እግዚብሔር የፈጠረው ሁለተናችንን ነው እንዲሁም የእኛም ተልዕኮ እግዚአብሔር የፈጠረውን የሰውን ሁለተና ማገልገል ነው፡ መንፈሱን፣ ነፍሱን እና አካሉ። የወንጌል ስርጭት፣ የርኅራሄ እና የፍትሕ ተልዕኮአችን የሰው ልጆችን አካላዊ፣ መንፈሳዊ እና ስሜታዊ ክፍሎችን ሁሉ ይዳስሳል።

ዓም አቀፍ ደረጃ ያለቸው ቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ለሰው ልጆች ሁሉ ልደርስ ይገባዋል ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው የእርሱን ስም የምጠሩ ሰዎችን ሁሉ ለማዳን ነው። እንደ እግዚብሔር ሕዝብ ማስማት ለምፈልጉ ሰዎች ሁሉ ወንጌልን መናገር በመቻላችን እድለኞች ነን እንዲሁም ኃላፊነት አለብን። በአደባቢ ስብከትም ይሁን አንድ ለአንድ ምስክርነት ጥረታችን ሰዎችን በክርስቶስ እንዲያምኑ መጋበዝ ብቻ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ወደ ዓለም ሁሉ የተሰራጨበት ምክንያት በጴንጤ ቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ በኃይል ስለወረደ ነው (ሐዋ 2)። ተልዕኮአችን በኢየሱስ በኩል የሚገኘውን ድነት ለዓም ሁሉ ማድረስ ነው። የእግዚብሔርን መንግስ መምጠትን ለማወጅ እና ቤተ ክርስቲያንን ከእግዚአብሔር ጋር ለመገንባት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተናል።

በዓለም ውስጥ እግዚአብሔር የሰጠንን ተልዕኮ ለመወጣት በብሩ ተስፋ ተነሳስተናል። ይህ ከሰው ልጆች አቅም እና ጥረት በላይ የሆነ ነገር ነው። ተልዕኮአችን ለእግዚብሔር ጥር ምላሽ መስጠት ነው። ይህ በእግዚአብሔር መንግስት የማስታረቅ ተልዕኮ ውስጥ የሚደረግ ተሳትፎ ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ፍቅር በታማኝነት ለሰዎች ሁሉ ለማካፈል የምታደርገው ጥረት ነው፡ ይህም በወንጌል ስርጭት፣ በርኅራሄ አገልግሎት እና ለፍትም በመቆም ይገለጣል። ይህ በኃጢአት ምክንያት ሕይወታቸው የተሰበሩ ሰዎችን ለመለወጥ እና የእግዚአብሔር መልክ በውስጣቸው እንድታደስ ለማድረግ በእግዚብሔር ጸጋ የሚሠራ ሥራ ነው።

**3ሐ. ሰዎችን ደቀ መዛሙር የማድረግ ተልዕኮአችን**

ራሳችን የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በመሆን ሌሎች እንዲሆኑ እንጋብዛለን። ይህንን ታሳብ በማድርግ ይህ የምቻልበትን መንገድ እናመቻቻላን (በሰንበት ትምህርት፣ በመጸሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ወዘተ)። በእነዚህ መንገዶች አማኞች ክርስቲያናዊ እምነትን በማወቅ እንዲያድጉ ይደረጋል እንዲሁም እርስ በእርስ ባላቸው ግንኙነት እንዲሁም ከእግዚብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት እንዲያድጉ ይደረጋል። ደቀ መዝሙር መሆን ማለት እግዚአብሔርን መታዘዝ እና የእምነት ጉዞ መጓዝን እንደሚያካትት እንገነዘባለን። እርስ በእርስ በመተጋገዝ ቅድስና የተሞላበት ሕይወት ለመኖር፣ ሕብረት ላማድረግ ጥረት

እናድርጋለን። ዌዝል እንዲህ ብሎ ነበር ‹‹እግዚአብሔር እንዳችን ሌላኛችንን ለማበረታታት ይረዳን ዘንድ ለእያንዳንዳችን የሌላኛውን እጅ ሰጥቶናል።››

ክርስቲያናዊ ደቀ መዝሙርነት የሕይወት ዘይቤ ነው። ይህ እግዚአብሔት በምድር ለይ እንዴት እንድንኖር እንደሚፈለግ መማሪያ ሂደት ነው። የእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ መኖርን፣ በእምነተ በመገዛት መኖርን ስንማር እና እርስ በእርሳችን መገዛትን እየተማር ስንመጣ የደቀ መዝሙርነት ሕይወት እውነተና ደስታን መለማመድ እንጀምራለን  እንዲሁም ክርስቲያናዊ ነጻነት ትርጉም ምን እንደሆነ እንገነዘባለን። ደቀ መዝሙርነት የሰው ልጅ ጥረት፣ ለሕግጋት መገዛት ብቻ አይደለም። ደቀ መዝሙርነት መንፈስ ቅዱስ  በሂደት ወደ ክርስቲያናዊ ብስለት የሚያመጣበት መንገድ ነው። በዚህ የደቀ መዝሙርነት የመሆኛ መንገድ ነው የክርስቲያኖችን ባሕርይ የምንላበሰው። የደቀ መዝሙርነት የመጨረሻው ግብ የክርስቶስን መልክ መምሰል ነው (2 ቆሮ 3:18)

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እና በማሰላሰል ክርስቲያኖች በደቀ መዝሙርነት ጉዞዋቸው ከማያቋርጥ ጅረት ይረሰርሳሉ። በእግዚአብሔር ቃል እየታጠቡ፣ በእግዚአብሐየር ቃል እየነጠሩ፣ የእግዚብሔር ቃል እውነት እየጠጡ ደቀ መዛሙርቱ ‹‹በአእምሮዋቸው መታደስ›› በመለወጥ የሚገኘውን ደስታ ጣጥማሉ (ሮሜ 12:2)። ጥናታዊ የጸሎት፣ ጾም፣ የአምልኮ፣ የአገልግሎት ደቀ መዝሙርነት መንገዶች ሁሉ እንቀበላለን።

ደቀ መዝሙርነት መተጋገዝንና አንዱ ሌላኛውን መቆጠጥር ያካትታል። በግላቸው ወደ ክርስቲያናዊ ብስለት የሚያመራውን ደቀ መዝሙርነት ሂደት መጓዝ የሚችሉት ጥቂቶች ናቸው። በሰንበት ትምህርት፣ በደቀ መዝሙርነት ቡድን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ቡድን፣ በጸሎት ስብሰባ ወዘተ እርስ በእርስ በመተጋገዝ ይህንን መፈጸም ይቻላል።

### 3መ. ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለን ተልዕኮ

ክርስቲያን ወንዶች እና ሴቶች ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ራሳቸውን ብቁ ለሚያደርጉበት ለክርስቲያናዊ ትምህርት የተሰጠን ነን። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶቻችን፣ በከፈተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን እና ዩንቨርስቲዎቻችን ውስጥ ሰዎች እውቀት እንድገበዩ፣ ክርስቲያናዊ ባሕርይን እንድያጎለብቱ እንዲሁ እግዚአብሔር የሰጠንን ተልዕኮ ለመወጣት መሪዎችን ለማፍራት ተግተብ እንሠራለን።

በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቲያናዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጉዳይ ማዕከላዊ ነው። በናዛሪን ቤተ ክርስቲያናት ቀደምት ዓመታት የናዛሪን የትምህርት ተቋማት ወንዶችን እና ሴቶችን ለመሪነት እና ክርስያናዊ አገልግሎት በማስታጠቅ የዌዝልያን ቅድስናዊ መልዕክት እድያሰራጩ እገዛ አድረገዋል። በምቀጥሉት ዓመታት ይህንን ጥረታችንን በመቀጠል የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች እና ዩንቨርስቲዎች ህብረትም እንጀምራለን።

ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለን ተልዕኮ የሚመነጨው የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆን ማለት ምንድ ነው ከሚለው ነው። እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን፣ ነፍሳችን እና አእምሮዋችን መውደድ ይጠበቅብናል። ስለዚህም አእምሮዋችን፣ በጥሩ ትምህርታዊ ነገር ማዳበር እና እንደ ጥሩ ባለአደራ መንከባከብ ይጠበቅብናል። በዚህም መሠረት ግልጽ እና እውነተኛ እውቀትን ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን እንዲሁም ከክርስትና እምነት ጋርም ይህንን ለማያያዝ ጥረት እናድረጋለን። ክርስትያናዊ ከፍተና ተቋማት አእምሮዋችን እንደ ባለአደራ ለመጠቀም በጣም ጥሩ ስፍራ ነው። እውነተን በመፈለግ

እና ስለ እውነት መወያየት የሚቻልበት ስፍራ ነው፤ ስለ እግዚአብሔር እና እርሱ ስለፈጠራቸው ፍጥረታት እውቀት የሚገበይበት ስፍራ ነው።

በክርስቲያናዊ ከፍተኛ ተቋመማት ውስጥ እምነት ተገሎ ለብቻው አይቀመጥም ነገር ግን ጥሩ በሆነ ሁኔታ ከእውቀት ጋር ተዋህዶ በአንድነት ያድጋሉ። ሙሉ የሰው ልጅ ማንነት ተኮትኩቶ የሰው ልጅ እግዚአብሔር ባዘጋጀው መንገድ ያድጋል። ክርስቲያናዊ ባሕርይ እና ክርስቲያኖችን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ማስታጠቅ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ይህ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለዚህ አገልግሎት መስጠት ክርስቲያን ወንዶችና ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ በዓለም ሁሉ ያላቸውን ተልዕኮ ለመወጣት እጅግ ወሳኝ ነው።

ክርስቶስን ለመምሰል እንደተጠራ የተዋጀ ሕዝብ እና በዓለም ውስጥ የእግዚአብሔር ወክል ለመሆን እንደ ተላከ ሕዝብ የሰው ልጆችን በመዋጀት ሂደት ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር እንሳተፋለን። ክርስቲያናዊ ከፈተኛ የትምህርት ተቋማት ተልዕኮአችን በመፈጸም ሂደት ውስጥ ከፍተኛ እገዛ ድርጉልናል። በተለያየ የሙያ ዘርፍ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ውጤታማ እንሆነ ዘንድ በጣም ብዙ ዓይነት እውቀት ያስጨብጡናል። በእግዚአብሔር ሰዎችን የመዋጀት ሂደት ውስጥ በታማኝነት ለመሳተፍ ወንዶችና ሴቶችን በቤተ ክርስቲያንም ይሁን በዓለም ውስጥ መሪ አድርጎ ማስነሳትን ይጠይቃል።

ልናገለግለው የተጠራነው ዓለም በየዕለቱ እርስ በእርሱ እየተያያዘነ እየተወሳሰበ መጥቷል። የእግዚአብሔር ሰዎችን የመዋጀት ሥራው ዛሬ እና ለወደፊት እየሰፋ ሲሆን የከፍተኛ የትምህርት ቋማት አስፈላጊነት የግድ ይላል።

### ማጠቃለያ

በ20ኛ ክፈለ ዘመን መገባደጃ ላይ የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ተወለደች! ፒ.ኤፍ. ብሪይስ እና ሌሎች እግዚብሔር የኢየሱስን ክርስቶስን ወንጌል በዌዝሊያን የቅድስና ትውፊት መሠረት ለቤተ ክርስቲያናትና ለዓም ሁሉ ለመናገር እንዳስነሳቸው ከልባቸው አመኑ። ያለስህተት እነዚህ ሰዎች በዚህች ቤተ እምነተ ላይ የጣት አሻራቸውን አኑረዋል። የናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ከትንሽ ንቅናቄ ዛሬ 1.3 ሚልዬን የሚሆኑ አባላት ያሉበት እና በ119 ሀገራት ውስጥ የሚገኝ አገለግሎት ሆኗል።

በ21ኛ ክፈለ ዘመን መግቢያ ላይ የዚህች ቤተ እምነተ የወደፊት ዕጣ ፈንታ እንዲህ ብሩህ ሆኖ አያውቅም! ብዙዎች እኛን እግዚአብሔር ያስነሳን ለ20ኛው ክፍለ ዘመን ሳይሆን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ያምናሉ። በዚህ ድህረ ዘመናዊው ዓለም ውስጥ እኛም የራሳችንን ድርሻ ለመወጣት ራሳችንን አዘጋጅተናል። ይህ እምነታችን በዌዝሊያን የቅድስና ባህላችን ውስጥ ይነጸባረቃል። በእግዚአብሔር ጸጋ አማካኝነት የሰው ልጅ ባህርይ እንዲሁም በመጨረሻም አንድ ማህበረሰብ ፈጽሞ ለለወጥ ይችላል ብለን እናምናን። በዚህ ከእግዚአብሔር ቅዱስ ልብ ውስጥ በሞመነጨው የተስፋ መልዕክት ትልቅ መተማመን አለን።

ፒ.ኤፍ. ብሪይስ እንዲህ ይል ነበር ‹‹ፀሐይ ፈጽሞ በጥዋት አትጠልቅም››። በናዛሪን ቤተ ክርስቲያን ዘንድ አሁንም ጥዋት ነው እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሉ ቤተ ክርስቲያኖቻችን አሁንም ቢሆን ገና ጥዋት ነው። በቅድስና መልዕክት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ተጽእኖ መፍጠር እንችላን የሚል ብሩህ የሆነ ተስ አለን። ግልጽ በሆነ ራዕይ፣ ፈጽሞ መስጠት እና ጠንካራ እምነት መጭው ምእተ

ዓመትከሁሉም ሀገራት ክርስቶስን የሚመስሉ ደቀ መዛሙርትን የምናፈራበት እንደሚሆንልን እምነታችን ነው፡፡